የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 16
ADDIS ABABA-13th January,2004


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፩/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዮት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ................... ገጽ ፪ሺ፭፻፳፫


### አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፩/፲፱፻፺፮

### የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዮት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዮት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፩/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ማሻሻያ

የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዮት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺ /እንደተሻሻለ/ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·80

## CONTENTS


Proclamation No. 381/2004

Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment /Amendment/ Proclamation ... Page 2523


### PROCLAMATION NO. 381/2004.

### A PROCLAMATION TO AMEND THE INSTITUTE OF BIODIVERSITY CONSERVATION AND RSEARCH ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**
   This Proclamation may be cited as the "Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment (Amendment) Proclamation No. 381/2004."

2. **Amendment**
   The Institute of Biodiversity Conservation and Research Establishment Proclamation No 120/1998 (as amended) is hereby further amended as follows:


ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ በአዋጁ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት" የሚለው ስያሜ ተሰርዞ "የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት" በሚለው ተተክቷል::

፪/ በአዋጁ የአማርኛው ቅጅ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ሕይወታዊ ሀብት" የሚለው ተሰርዞ "ብዝሀ ሕይወት" በሚለው ተተክቷል::

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፯/ ተጨምሯል፤

"፯/ "የብዝሀ ሕይወት ናሙና"ማለት የዕፅዋት፣ የእንስሳት ወይም የጥቃቅን ህዋሳት ዘረመል ወይም ዝርያ ናሙና ማለት ሲሆን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፮/፲፱፻፺፬/ በአዋጅ ቁጥር ፫፻፹/፲፱፻፺፮ እንደተሻሻለ/ አንቀጽ ፰/፫//ሀ/ በተመለ ከተው ትርጓሜ የሚሸፈን የግብርና ግብዓትን አይጨምርም::"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተተክቷል::

"፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል::"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ /፭/ ተተክቷል::

"፭. <u>ዓላማ</u>
የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የሀገሪቱ ብዝሀ ሕይወት በአግባቡ መጠበቁንና ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ይሆናል::"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ /፮/ ተተክቷል::

"፮ <u>ሥልጣንና ተግባር</u>
ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1/ The designation "Institute of Biodiversity Conservation and Research" appearing anywhere in the Proclamation is deleted and replaced by the "Institute of Biodiversity Conservation."

2/ The English version of the word "Biological Diversity" appearing anywhere in the Proclamation has been deleted and replaced by "Biodiversity.

3/ The following new Sub-Article (7) is added under Article 2 of the Proclamation:

"7/ biological specimen/sample" means the specimen/sample of plant, animal or micro-organisms genes or species and does not include agricultural inputs as defined under Article 8(3) (a) of the Reorganization of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 256/2001 (as amended by Proclamation No.380/2004)."

4/ Sub-Article (2) of Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2/ The institute is accountable to the Ministry of Agriculture and Rural Development."

5/ Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 5:

"5. **<u>Objective</u>**
The objective of the Institute is to ensure the appropriate conservation and utilization of the country's biodiversity."

6/ Article 6 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 6:

"6. **<u>Powers and Duties</u>**
The Institute shall have the following powers and duties to:

፩/ የሀገሪቱን ብዝሀ ሕይወት ጥበቃ የሚመለከቱ የፖሊሲና የሕግ ሃሳቦችን ማመንጨትና ሲፈቀዱም ሥራ ላይ ማዋልና መዋላቸውን መከታተል፣

፪/ በሀገሪቱ የሚገኘውን የዕፅዋት፣ የእንስሳትና የጥቃቅን ሕዋሳት ሀብት ተለያይነትና ሥርጭት በመቃኘትና በማሰስ ለኢዘቦታ ጥበቃ የሚውሉትን መሰብሰብ፣ ማንበርና ለምርምርና ልማት ሥራዎች ጠቀሜታ የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

፫/ የሀገሪቱን ብዝሀ ሕይወት ለመጠበቅ የዘቦታና ኢዘቦታ ጥበቃ ዘዴዎችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

፬/ በተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት የብዝሀ ሕይወት የተመናመነባቸውን አካባቢዎች በማጥናትና በመለየት ቀደም ሲል ከተሰበሰበውና በኢዘቦታ ጥበቃ ከሚገኘው ዘረመል በመጠቀም ተመልሶ እንዲተካ ለሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ ማቅረብና ተቀባይነት ሲያገኝም ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ድጋፍ መስጠት፣

፭/ ሀገሪቱን ለልማት ሊውል በሚችል ተጨማሪ ብዝሀ ሕይወት ለማበልጸግ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን ከውጭ ማስመጣትና ቀደም ሲል ከሀገር የወጡትን ዝርያዎች በሚመለከትም ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ለማስከበር የሚያስችሉ እርምጃዎችን አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት መውሰድ፣

፮/ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ብዝሀ ሕይወትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

፯/ ብዝሀ ሕይወት ጥበቃን በሚመለከት ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመተባበር መስራት፣

፰/ ሀገሪቱ በባለቤትነት የምትታወቅባቸውን የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎች በመመዝገብና በተለይም ለጥፋት የተጋለጡትን በማናት የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

1/ initiate policy and legislative proposals on conservation of the country's biodiversity and, upon approval, enforce and follow up their implementation;

2/ explore and survey the diversity and distribution of the country's plant, animal, and microbial genetic resources; collect samples for ex-situ conservation and facilitate utilization of these genetic resources for research and development;

3/ ensure the conservation of the country's biodiversity using ex-situ and in-situ conservation methods;

4/ identify and study localities where man-made and natural calamites are causing genetic erosion and from such assement recommend, to the concerned bodies, the restoration of the lost materials in the locality from the ex-situ conserved germplasm and, upon its endorsement, facilitate and support its implementation;

5/ enrich that part of the country's biodiversity which can be utilized for its development through introduction of germplasm from international sources, and take appropriate measures based on international agreements to protect the interests of the country with regard to germplasm of Ethiopian origin and previously taken out of the country;

6/ implement, in cooperation with the concerned bodies, treaties on biodiversity to which Ethiopia is a party;

7/ work in cooperation with the concerned federal and regional bodies with respect to conservation biodiversity;

8/ register germplasm of Ethiopian origin and undertake studies, in particular, on those threatened by extinction to develop a strategy for their conservation;

፱/ የሀገሪቱን ብዝሀ ሕይወት መጠንና ሥርጭት የሚያበለጽጉ ወይም የሚያናጉ ክስተቶችን አስቀድሞ በመተንበይ ጤናማ ሂደቶችን ለማስቀጠልና የችግር ስጋቶችን ለመገደብ የሚያስችሉ የፖሊሲ ሃሳቦችን ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፤

፲/ የብዝሀ ሕይወት ጥበቃን በሚመለከት ከአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር መተባበር እና ሀገሪቱ በብዝሀ ሕይወት ሀብቷ ላይ ያላትን የሉዓላዊነት መብት ለማረጋገጥና ጥቅሟን ለማስከበር የሚያስችሉ ርምጃዎችን አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሀገሪቱ ሕጎች መሠረት መውሰድ፤

፲፩/ የሀገሪቱ ብዝሀ ሕይወት የሚጠበቅበትን ሥርዓትና የቴክኒክ ብቃት በማጥናትና በመወሰን የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በሚገባ እንዲገነዘቡት ማድረግ፤

፲፪/ የብዝሀ ሕይወት ናሙና ለመሰብሰብ፣ለማሰራጨት፣ ወደ ውጭ አገር ለመላክና ከውጭ አገር ለማስመጣት የሚያስችል መመሪያ ማውጣትና ፈቃድ መስጠት፤

፲፫/ ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ መወሰንና መሰብሰብ፤

፲፬/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤

፲፭/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮች ማከናወን::”

፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፰ ተሠርዞ ከአንቀጽ ፱ እስከ ፲፯ እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፰ እስከ ፲፮ ሆነዋል::

፰ በአዋጁ አንቀጽ ፰ /የቀድሞ አንቀጽ ፱/ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ውስጥ “በቦርዱ አቅራቢነት” እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ /፪/ ውስጥ “ከቦርዱና በቦርዱም አማካይነት ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት” የሚሉት ሐረጎች ተሰርዘዋል::

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፰ /የቀድሞው አንቀጽ ፱/ ንዑስ አንቀጽ ፫ /ረ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫ /ረ/ ተተክቷል፤

9/ identify processes that promote or threaten the existence of the country's biodiversity resources; formulate and propose policy ideas to concerned authorities which enable to promote the healthy processes and control the threatening ones;

10/ develop regional and international cooperation in biodiversity conservation activities, and based on international agreements and national legislation take appropriate action to maintain the sovereign rights of the country over its biodiversity;

11/ study and develop systems and technical standards for the conservation of the country's biodiversity and create awareness on same among all concerned;

12/ issue directives on the collection, dispatch, import and export of any biological specimen/sample and give permit to collect, dispatch, import or export same;

13/ determine and collect commensurate fees for services it renders;

14/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

15/ perform such other duties as are conducive to the attainment of its objectives."

7/ Article 8 of the Proclamation is deleted and Articles 9-17 are renumbered as Article 8-16 respectively.

8/ The phrases "upon the recommendation of the Board" in Sub-Article (1) and "subject to the general directives of the Board, and through the Board from the Ethiopian Agricultural Research Organization" in Sub-Article (2) of Article 8 (the former Article 9) of the Proclamation are deleted.

9/ Sub-Article 3(f) of Article 8 (the former Article 9) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article 3(f):

"ረ/ የኢንስቲትዩቱን ሪፖርት አዘጋጅቶ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፤ እንዲሁም የብዝሀ ሕይወት ዓለም አቀፍ ስምምነት አፈጻጸምን በሚመለከት ዓመታዊ ሪፖርት ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

፫/ <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

"f/ prepare and submit to the Ministry of Agriculture and Rural Development the reports of the Institute; and submit to the Environmental Protection Authority annual reports on the implementation of the Convention on Biological Diversity.

3. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the 13th day of January, 2004

**Done at Addis Ababa, this 13th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**